

# ~1~

# “ሄሎ እግዚአብሔር!”

## 1-1

ጊዜው ከፉ ነው። ዘመን አልፎ ዘመን ሲተካ በዚያው ልክ ሁኔታዎችም ይለዋወጣሉ። ትላንት እንደዛሬው አይደለም፤ ዛሬም እንደ ነገር አይሆንም። ዓለማችን እየከፋች እንጂ ደግ እየሆነች አትሄድም። የልብ ስብራት የደረሰባቸው፣ ሃዘን ሕይወታቸውን ያጨለመባቸው ሰዎች ቁጥራቸው ትንሽ አይደለም። ብዙዎች ተስፋ መቁረጥ ልባቸውን ሞልቶታል። ፍርሃት አስጨንቋቸዋል። የብዙዎች ደም እንደ ውሃ በከንቱ ይፈሳል። ረሃብና ቸነፈር የሰውን ዘር ከምድር ገጽ ለማጥፋት ይታገላል። በረሀብ፣ በጦርነትና በልዩ ልዩ ምክንያት ከእናት አገሩ እየተፈናቀለ ስደተኛ ሆኖ የሚኖረው ህዝብ ቁጥር በቀላሉ የሚገመት አይደለም። ህጻናት በረሃብ ሲያልቁ፣ ጎልማሳው ተፈጥሮ ሳይተባበረው በመቅረቱ መሬት ቆፍሮ ኑሮውን ማሸነፍ አቅቶት ሜዳ ለሜዳ ሲንከራተት ማየት ልብን ይሰብራል።

የገንዘብም አቅም ያላነሰው ደግሞ ሕይወቱ በሌላ በኩል ተነክቷል። ትዳሩ ነቀዝ የበላው ዛፍ ይመስል ተቦርቡሮ አልቆ የቆመው በቋፍ ላይ ነው። ወንድ ልጁ ከድቶት ሄዶ ሜዳ ለሜዳ ይዋልላል፤ ሴት ልጁም ሳታገባ አርግዛ ሰው እንዳያያት “የለችም ጸበል ሄዳለች” ተብሎ ይወራል። የዚህ ሁሉ ምክንያት “አንተ ነህ” የለም “አንቺ ነሽ” በመባባል ኑሮአቸውን በጭቅጭቅ የሚገፉት ቤተሰቦች ብዙ ናቸው። የብዙዎች ልብ በሀዘን ሲሰበር፣ በጦርነት ምክንያት የፈራረሰን ሥጋ አራዊት ሲበላው፣ ህጻናት በረሀብ ሲያልቁ፣ ጎልማሳው ሥራ አጥቶ ሲንከራተት፣ የቤተሰብ አቋም ሲናጋ፣ ስደተኛው በበረሃና በባዕድ አገር ሲንከራተት ያየ ሰው “ለመሆኑ እግዚአብሔር ይሄ ሁሉ ሲሆን የት ሄዷል? አሁንስ የሰውን የጭንቀት ድምጽ መስማት ይችላልን?” ብሎ መጠየቁ አይቀርም። ኑሮው ብርቱ ትግል የሆነበት ክርስትያን “አሁንስ ይህንን ክርስቶስ ባገኘው ኖሮ እነግረው ነበር” ሲል ይሰማ ይሆናል። እርግጥ ነው ሁኔታው ያሰኛል። ታዲያ ለምን አንነግረውም? “መንገሩንስ እንነግረዋለን ሆኖም ጸሎታችንን ይሰማል ወይ?” የሚለውን ጥያቄ መጠየቃችን አይቀርም። *“እናንተም ትጠሩኛላችሁ፥ ሄዳችሁም ወደ እኔ ትጸልያላችሁ፤ እኔም እሰማችኋለሁ። እናንተ ትሹኛላችሁ፣ በፍጹም ልባችሁም ከሻችሁኝ ታገኙኛላችሁ”* ኤርሚያስ 12-13።

## ጸሎትን የተለማመደው ያውቀዋል

የጸሎትን ኃይል የሚያውቀው የጸሎትን ሕይወት የተለማመደ ብቻ ነው። የውሃ ዋና ለሰውነት እንቅስቃሴ ጠቃሚ መሆኑን ሲነገር እንሰማለን። ታዲያ ይሄ እውነት መሆኑን ማረጋገጥ የሚቻለው ዋኝቶ ያየው እንጂ እግሩን ውሃ ውስጥ ለመንከር የሚፈራው ሰው አይደለም። እንዲሁም ከወዳጃችን አንዱ በጣም ቢታመምብን የህክምና ትምህርት ያልነካውን ሰው አክምልን ብለን አንጠራውም። እንደዚሁም እኛ የጸሎትን ኃይል በግል ያልተለማመድን ከሆነ እውነተኛነቱን መናገር ያቅተናል። ስለዚህ የጸሎትን ኃይል ለመረዳት በሕይወታቸው የጸሎት ሕይወትን የተለማመዱትንና መልስ ያገኙትን ሰዎች መጠየቅ ወይንም ታሪካቸውን ማወቅ ይጠቅመናል። አብርሃም እግዚአብሔር ልጅ

እንዲሰጠው ለመነ። አብርሃም ባልጠበቀውና ይሆናል ብሎ ባልገመተበት ጊዜ ይስሃቅን ሰጠው፤ ዘሩንም እንደ ሰማይ ከዋክብት አበዛ። ሙሴ፣ ኢያሱ፣ ጌዲዮን፣ ሳሙኤል፣ እንዲሁም ሌሎች ታላላቅ የእግዚአብ ሔር ሰዎች ወደ እግዚአብሔር ቀርበው በጸሎት ልባቸውን አፈሰሱለት። እርሱም ጸሎታቸውን ሰማ።

## ጸሎት ለምንድነው?

ጸሎት ለአንዳንዶች ሁልጊዜ የሚደረግ ሳይሆን በወር ወይንም በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ የሚሆን ነው። ያም የሚሆነው ምናልባት ክርስትያኖች ወደ ቤታቸው የመጡ እንደሆነ ይሆናል። ለብዙዎች ደግሞ ጸሎት "ድንገተኛ መድኃኒት" ወይንም "ባጣ ቀረኝ" ዓይነት ነው። ይኸውም የኑሮ ግፊት ሲያይል፣ አንዳንድ ሁኔታዎች እንደጠበቁት ሆኖ ሳይገኝ፣ በኑሮአቸው መጎሳቆል ሲጀምሩና እንዲሁም የራሳቸው መንገድ ሲጠብባቸው ያኔ ብቻ "እስቲ ጸሎት የሚሉትን ነገር ልሞክረው" ብለው ይጸልያሉ። ሁኔታዎች እንደገና ሲስተካከልላቸውና እነርሱም በሁለት እግራቸው ሲቆሙ ጸሎትን መልሰው ይተዉታል። ለአንዳንዶች ደግሞ ጸሎት ህግ ወይንም ደንብ ብቻ ነው። በዚህ የተነሳ ሥርዓት ለማድረስ ብቻ ደስ ሳይላቸው ወደ ጸሎት ይሄዳሉ። ወደ ጸሎት ከመሄድ ይልቅ መራራ መድሃኒት መዋጥ ይቀላቸዋል። "መልካሚ የጸሎት ሰዓት" ብለው የሚናፍቁት ጊዜ አይደለም። ለአብዛኞች ሰዎች ደግሞ ጸሎት የቃላት ጨዋት ብቻ ነው። ምላሳቸው የሚያወራውን ልባቸው በፍጹም አያውቀውም። ከልብ ፈንቅሎ የወጣ ጸሎት ሳይሆን ተራ "ድግምት" ብቻ ነው። ከዚህም በኋላ "ብዙ ጸለይኩ ቢሆንም ሌሎች እንደሚሉት ጸሎት አልረዳኝም" ይላሉ። የጸሎት ትክክለኛ ትርጉም የገባቸው ደግሞ፥ ጸሎት የመንፈሳዊ ሕይወት አውታር እንደሆነ ያዩታል። ያለምግብ ሰውነታቸው እንደማይንቀሳቀሰው ሁሉ መንፈሳዊ ሕይወታቸውም ያለ ጸሎት መንቀ ሳቀሳ እንደማይችል ያምናሉ።

**በሚቀጥለው ክፍል፥ እምነት የጸሎት ቁልፍ፣ ጸሎት ከልብ እንደሚፈልቅና ጸሎት ለምን እንደሚጠቅም እንመለከታለን።**

**የጌታ ጸጋና ሰላም ከእናንተ ጋር ይሁን። እሜን!**